# በጥገኝነት ጥያቄዎ ላይ አዎንታዊ ውሳኔ ሲያገኙ

**በጥገኝነት ጥያቄዎ ላይ አወንታዊ ውሳኔ ከተቀበሉ በኋላ ምናልባት ብዙ የሚያስቡበት ነገር እንዳልዎት እናውቃለን። እነዚህም የመማር፡ የመስራት ወይም የምታስቡላቸውን ሰዎች ለማየት የመጓዝ እቅድዎን ሊያካትቱ ይችላሉ። ውሳኔዎን ከተቀበሉ በኋላ የጥገኝነት ድጋፍዎ ከማብቃቱ በፊት ትንሽ ጊዜ ብቻ ነው የሚኖርዎት ስለዚህ በመጀመሪያ በእነዚህ ሶስት ነገሮች ላይ ማተኮር አስፈላጊ ነው።**

## 1. የሁኔታ እና የመታወቂያ ማረጋገጫ - የእርስዎ ኢቪዛ

- ዩኬ ወደ ዲጂታል የኢሚግሬሽን ስርዓት እየተሸጋገረች ነው። ከኦክቶበር 31፡ 2024 ጀምሮ፡ ሆም ኦፊስ ከባዮሜትሪክ የመኖሪያ ፈቃዶች (BRP) ይልቅ ኢቪዛዎችን መስጠት ጀምሯል።
- ኢቪዛዎ በጣም አስፈላጊ ነው። ስራ ለማግኘት ወይም ጥቅማጥቅሞችን (ቤኔፊት) ለመጠየቅ እና የመኖሪያ ቦታ ለመከራየት ያስፈልግዎታል።
- ሆም ኦፊስ የዩኬ ቪዛ እና ኢሚግሬሽን (UKVI) መለያዎን እና የኢቪዛዎን የእርስዎ አዎንታዊ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በ14 ቀናት ውስጥ ይፈጥራል። መለያዎን እና ኢቪዛዎን ለመድረስ የሚፈልጉትን የመግቢያ መረጃ ይልክልዎታል።
- የ UKVI መለያ ዝርዝሮችን ካልደረስዎ ወይም ኢቪዛዎን ለመድረስ እርዳታ ከፈለጉ እባክዎን UKVI Resolution Center ያነጋግሩ። የእነርሱን የኦንላይን ዌብቻት በመጠቀም (ወደ www.gov.uk/evisa ይሂዱ እና "እርዳታ ከፈለጉ" (“If you need help”) የሚለውን ይጫኑ) ወይም ማይግራንት ሀልፕን በ 07483 170100 ወይም በ evisa@migranthelpuk.org ያግኙ።
- ኢቪዛዎ ላይ ስህተቶች ካሉ፡ እባክዎን UKVIን በwww.gov.uk/report-error-evisa ያግኙ።

## 2. ገንዘብዎ

- አወንታዊ ውሳኔ ካገኙ በኋላ ሰርተው ገንዘብ እንዲያገኙ ይፈቀድልዎታል።
- መስራት ካልቻሉ ወይም ስራ በፍጥነት ማግኘት ካልቻሉ፡ ለደህንነት ጥቅማጥቅሞች (በተለምዶ ዩኒቨርሳል ክሬዲት) ማመልከት አለብዎት። በኦንላይን ላይ ወይም በአከባቢዎ በሚገኘው ጆብ ሴንተር ፕላስ በአካል በመቅረብ ማመልከት ይችላሉ።
- ክፍያዎችዎን ከመቀበልዎ በፊት የተወሰነ ጊዜ ሊወስድ ስለሚችል ይህን ወዲያውኑ ያድርጉ።
- የባንክ ሂሳብ መክፈትም ያስፈልግዎታል።

## 3. የመኖሪያ ቤትዎ

- አወንታዊ ውሳኔ ካገኙ በኋላ፡ የራስዎን መኖሪያ ቤት መፈለግ መጀመር እና ወደዛም መሄድ ይችላሉ።
- የአካባቢዎን አስተዳደር (ውሳኔዎን ሲያገኙ ሚኖሩበት የነበሩበት ቦታ) እርስዎን እንዲረዳዎ መጠየቅ ይችላሉ። በአጠቃላይ ጤነኛ ከሆኑ እና ከእርስዎ ጋር የሚኖሩ ልጆች ከሌሉዎት ቅድሚያ መሰጠት እንዳለበት ሰው አይታዩም እና ምንም አይነት ማረፊያ ቤት ሊሰጡዎት አይችሉም። በአሁኑ ጊዜ ለሁሉም ሰው ከፍተኛ የማህበራዊ መኖሪያ ቤት እና የካውንስል ቤት እጥረት አለ።

### የመኖሪያ ቤት ኤቢሲ (ABC)

A መጀመሪያ - የሚያገኙት የመጀመሪያ ቦታ ለአጭር ጊዜ ብቻ ሊሆን እንደሚችል **ይቀበሉ**። ምናልባት ትንሽ፡ የጋራ ወይም ጊዜያዊ መጠለያ እንጂ መኖር በሚፈልጉት አካባቢ ላይሆን ይችላል።

B ቀጥሎ - የተወሰነ ገቢ እና/ወይም ስራ ካገኙ በኋላ፡ ወደሚፈልጉበት ቦታ ቅርበት ያለው፡ ነገር ግን ዋጋው ተመጣጣኝ የሆነ **የተሻለ** ቦታ መፈለግ ይችላሉ። እንደ የእንግሊዘኛ ትምህርት እና የቅጥር ድጋፍ ያሉ ነገሮች ይህን ለማድረግ ይረዱዎታል።

C በኋላ - ለረጅም ጊዜ መኖር ወደሚፈልጉት **ምቹ** ቤትን ለማግኘት ይስሩ።

SCAN ME

በአካባቢዎ ስላለው እገዛ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ድህረ ገጽ ለመክፈት የስልክ ካሜራዎን በዚህ ኪው አር (QR) ኮድ ላይ ይጠቁሙ።